# ዶክተር አብይ ፤የክልሎች ህጎችና የይቅርታ ጉዞ እንዴት?

አንቀጽ 2

'' በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦች የሚታውቁ ቢሆንም የክልሉ ባለቤት ብሔር ብሄረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ሽናሻ ማኦና ኮሞ ናቸው።''

ከላይ የምንመለከትው በ1995 ህዳር ወር ላይ የተሻሻለው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ህገመንግስት ነው። በዚህ ክልል ባለቤቶቹ አምስት ጎሳዎች ብቻ እንደሆኑ ይናገራል። እ ኤ አ በሁለት ሺህ ሰባት (2007) በተደረገው የቤቶችና ህዝብ ቀጠራ መሰረት በአጠቃላይ በክልሉ ሰባት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ሶስት መቶ አርባ አምስት (784, 345) ህዝብ ይኖራል።ከዚህ መካከል አንድ መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት (170,132) ማለትም ሃያ አንድ ነጥብ ሰባት ( 21.7) በመቶ አማራ ሲሆን አንድ መቶ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አምስት(106,275) ማለትም አስራ ሶስት ነጥብ አምስት (13.5) በመቶ ደግሞ ኦሮሞ ነው። የክልሉ ባለቤት እንደሆኑ ህገመንግስቱ እውቅና የሚሰጣቸው ጎሳዎች በአጠቃላይ የህዝብ ብዛታቸው 386,241 ነው። ማለትም ካጠቃላይ ነዋሪው 49.2 በመቶ ብቻ ሲሆን ቀሪው 51.8 በመቶ በክልሉ የሚኖር ህዝብ የክልሉ ባለቤት አይደለም። ። በነገራችን ላይ በዚህ ክልል በብዛት ከሚኖሩት ጎሳዎች አንደኛው በርታ ሲሆን ሁልተኛው አማራ ሶስተኛ ጉምዝ አራተኛ ደግሞ ኦሮሞ ናቸው።ሌላ አስገራሚና አስደናቂ ነገር የክልሉ ባለቤት ተብሎ በህገመንግስቱ እውቅና የተሰጠው ጎሳ ኮሞ በቁጥር 7,773 ብቻ ነው ። ይህንን በመቶኛ ብናስቀምጠው ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት 0.99 በመቶ ነው። ይህም ከ 1 በመቶ በታች መሆኑን ያሳየናል። አስቂኝ እንዲሆን በክልሉ ከሚኖሩት የአማራ እና ኦሮሞ ጎሳዎች ጋር ብናወዳድረው የአማራዉን 4.5 በመቶ የኦሮሞዉን ደግሞ 7.3 በመቶ ብቻ ናቸው።መስፈርቱ ከተለየ ፕላኔት የመጣ እንደሆነ አንጂ በምንም መስፈርት ማንበብና መጻፍ ለሚችል ህዝብ እንዲህ ያለ የአደባባይ ግልሙትና ባልተፈጸመ ነበር። እኩልነትን ፤ ዲሞክራሲን፣ ፍትህን ፤ነጻነትንና እድገትን ከሚሰብክ መንግስት ለምን እንደዚህ ፍርደ ገምድል የሆነ ህግ ይወጣል ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ በጣም ቀላል ነው። ባለቤት ያልሆነውን ህዝብ ለማባረር አስቀድሞ ኦርኬስትሬት የተደረገ መሆኑ ነው። ይህ አንቀጽ በዘፈቀደ የተጻፈ አይደለም ።የቤንሻንጉል ጉምዝ ህገመንግስት ማለትም በ1995 የተሻሻለው በአጠቃላይ 121 አንቀጾች አሉት። ይሁንና እያንዳንዱ አንቀጽ አግላይ ፣ ቆይቶ ቅሬታን የሚያስነሳ የግጭት መነሻና ማእከል የሚሆን ተራ ወረቀት ነው።ኢህአዴግ ብዙ ምሁራን አባላት አሉኝ በማለት ለዘመናት ሲያዎራ ኖሯል። ለረዥም ጊዜ የህግ መወሰኛ ምክርቤት ሰብሳቢ ሆነው ያገለገሉት አቶ አስመላሽ ምንም እንኳ ከትግል የመጡ እንደሆኑ ቢታዎቅም ይሄንን የመሰለ በህዝባችን አድልዎ ሲፈጸም ዝም ብለው ማየት አልነበረባቸውም። ታዲህ ህዝባችን ቤንሻንጉልና ሌሎች ክልሎችም የተመሰረቱት ከቋንቋ ባሻገር በገዥው መደብ ድብቅ አጀንዳና በተንኮል ነው ቢል የሚፈረድበት ለምንድን ነው? ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት መነሻ የሆነኝ ትግራይ ኦንላይን ላይ የተመሰረተውን አዲስ የ አማራ ንቅናቄ የሚቃዎም ጽሁፍ ካነበብሁ በኃላ ነው። በተለይም አማራው ሊመሰርተው የሚፈልገው ክልል በማላት ከጽሑፉ ጋር የወጣው ካርታ ትኩረቴን ሳበው። መጣጥፉን ላነበበ ብዙ የሚገባው ነገር እንደሚኖር አልጠራጠርም። ጽንፈኛው አማራ ይላል የትግራይ ኦንላይን ጸሐፊ '' ጽንፈኛው አማራ ከግማሽ በላይ ትግራይን፤ሙሉ በሙሉ አፋርን ፤ ሙሉ በሙሉ ቤንሻንጉልን፤አንድ ሶስተኛ ኤርትራን አሰብን ጨምሮና ስድሳ በመቶ ኦሮምያን ያካተተ መንግስት ለመመስረት ነው የሚታገለው '' ይላል። ጽሁፉ http://www.tigraionline.com/articles/amhara-

national-movement.html ላይ ይገኛል።ይህ ጽሑፍ ትኩረቴን ከሚገባ በላይ ሳበኝ። በተልይም የቤተ አማራ ተብሎ የወጣውን ካርታ በጥንቃቄ አስተዋልኩት። ምናልባት ከዚህ ጋር የተያያዘ አማራ ከእነዚህ አካባቢ የሚፈልገው ነገር ይኖርን ? በማለትም ራሴን ጠየቅሁ። ከዚያም የአማራ ድርጅቶች የማታገያ አላማቸውን ለመቃኘት ሞከርኩ ። ሁሉም በሚባል መልኩ አላማቸው አንድ ነው ። ''በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚኖር አማራ መብቱ እኩል ተከብሮ በነጻነት መኖር እንዲችል እንታገላለን፤ በእኩልነት የተመሰረተች አገር ለመመስረት አሁን ያለው የአማራ መገደል መታሰርና በማንነቱ መሰደድ እንዲቆም አንታገላለን።'' በቃ ጠቅለል ሲደረግ ይኸው ነው። ከዚያማ  አማራው መቶ በመቶ ሊዎስዳቸው ነው የተባሉትን ክልሎችና ህገመንግስቶቻቸውን ማየት ጀመርኩ። አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያውጣል አንዲሉ በአለም አቀፉ ህግ ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ብቻ ሳይሆን የዜጎችን አኩልነት ፈጽሞ የሚጻረር  ወንጀል ህገመንግስት ሆኖ አገኘሁት።ትግራይ ኦን ላይን ላይ ለምንድነው ቤንሻጉልን መቶ በመቶ አማራ ሊዎስደው ነው የሚል የስጋት አይሉት የማስጠንቀቂያ ደወል ያቃጨለው? እጅግ በጣም ቀላል ሰናሪዮ ማስቀመጥ ይቻላል። በክልልሉ ባለቤት መሆን የሚገባው በቁጥር በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠ ሆኖ እያለ  በሚገርም ተንኮል( በርግጥ ሳይንሳዊ አይደለም) ባለቤት አይደለም ተብሎ በህገመንግስት ደረጃ ተቀምጧል። ይህ መሰሪ ተንኮል መሆኑን የሚያዉቀው ያደረገው ብቻ ነው። አማራንና ኦሮሞን ለማግለል ተሰልቶ የተደረገው ይህ ህገመንግስት ጸሃይ ሲወጣ እንደሚታይ የተረዳው የትግራይ ኦን ላይን ጸሃፊ አማራ መቶ በመቶ ቤንሻንጉልን ሊዎስድ ነው በማለት አማራን የማባረሩ ሂደት አንዲቀጥል ያሳስባል። በመሰረቱ ለአስተዳደር እንዲመች ነው ቢባል እንኳ በምንም መስፈርት ለመተከል ከባህርዳር የተሻለ አማራጭ አልነበረዉም።የአንባቢዎቼን ትኩረት ለመሳብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ እውነታውን ለማሳየት በጎጃም ክፍለሀገር የመተከል አውራጃ ከነበሩት ሰባት አውራጃወች ሰፊውና አንደኛው ሲሆን የአሁኑ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል  የሚመካበት ሰፊና ለም የሆነ የእርሻ ቦታና የተፈጥሮ ሃብቶች አሉት። ከዚህ ቦታ ነው በተለይ የአማራ ዝርያ ያላቸው በማንነታቸው ብቻ ተለይተው ያፈሩትን ሃብትና ንብረት ሳይዙ ለቀው እንዲሄዱ የሚታዘዙት። ጎጃሜውን ከጎጃም ማባረር ማለት ነው። ለምን ተብሎ ቢጠየቅ አስቀድሞ የተወሰነና በህገመንግስቱም ከአምስቱ ጎሳዎች ውጪ ማንም ባለቤት ባለመሆኑ የሚል መልስ በቂ ይሆናል። ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ይህ ድርጊትና ህገመንግስቱ በራሱ የወንጀል ማስፈጸሚያ ፈቃድ ነው። እንዲሁ በደምሳሳው ስንመለከተው ህግን ስለማያዉቁ ያደረጉት የመሃይም ስራ ብቻ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን የተጠናና እቅድ በስራቱ የወጣለት በቅደም ተከተል የሚከናዎን  በመሰሪያዊ አካሄድ የታጀበ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ ልጨምር።በዚህ አድራሻ የምናገኘው መጣጥፍ ጠንከር ያለና ምናልባትም የፒኤችዲ የምርምር ጽሑፍ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

https://openaccess.leidenuniv.nl/bitstream/handle/1887/13839/chapter%20nine.pdf?sequence=6  ከአድራሻው መመልከት እንደሚቻለው ተራ ጽሁፍ አይደለም። በኔዘርላንድስ የሚገኝ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ ማለም የላይደን ዩኒቨርስቲ  ንብረት  እንደሆነ ያስረዳል። በአጠቃላይ በጉሙዝ ጎሳ አማራና ኦሮሞ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ይዘረዝራል። ጽሑፉ በኦንላይን  የተቀመጠው በከፊል ነው።

The formation of the BGNRS has indeed transformed relationships between the Gumuz and their neighbours. One important aspect in these relationships is the process of making inter-regional boundaries, which is fraught with friction and tension. This is particularly important for the emerging relationship between the BGNRS and Oromia regions. Regarding Gumuz-Amhara relations, the formation of the BGNRS appears to have effectively changed the frontier nature of their relationship. In spite of this, the presence of a large number of ethnic Amhara within the BGNRS

region and their continuous migration to the latter influence their relationships. የቤንሻንጉል ጉምሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መመስረት የጉሙዝ ጎሳ ከጎረቤቶቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ቀይሮታል። አንደኛው አስፈላጊ ጉዳይም በውጥረትና በፍርሃት የተሞላውን በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ማካለሉ ነው። ይህ በተለይም ከኦሮሚያ ጋር ላለው ግንኙነት አስፈላጊ ነው። ጉሙዝ ከአማራ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምስረታ የፊት ለፊት ተዋናዩን ውይም የጨዋታው ዋና ማን እንደሆነ ለይቶታል። ቢሆንም ግን በክልሉ በርካታ ቁጥር ያለው አማራ ስለሚኖር አሁንም እየፈለሰ መምጣቱ የክልሎችን ግንኙነት ተጽኖ አድርጎበታል በማለት አማራ ክልሉን እንዴት በተጽእኖው ስር እንዳደረገው ይዘረዝራል። በነገራችን ላይ ይህ ጽሑፍ ቤንሻንጉል ጉምዝን የጉሙዝ አገር በማለት ይጠራዋል። በተጨማሪም አማራ በስደት ይመጣል ይላል። ጠለቅ ብለን ስናነብበው የጉሙዝ ዲሞግራፊ በአማራ ተጽእኖ አንዳይቀየር በማለት መወሰድ ስለሚገባው እርምጃም ያወራል። ይህ መርዘኛ ጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ከአድራሻው ማየት እንደሚቻለው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከትግራይ ጋር እንደሚዋሰንም ምንጩ በመጥቀስ ካርታውን አስቀምጦታል።

እነዚህን በጣም ጥቂት ነገር ግን ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ሳቀርብ የዶክተር አብይን የይቅርታና ምህረት ጉዞ ለማደናቀፍ ሳይሆን የጀመሩት ጉዞ ቅንነት ያለበት እስከሆነ ድርስ በሀገሪቱ የተንሰራፋዉን የአድልዎ፣ መሰሪነትና ዘረኝነት ሰነዶች እገዳና ማእቀብ እንዲያደርጉ ለማሳሰብ ነው። እስኪ ይታያችሁ ሰው በሃገሩ ባለቤት አይደለህም ፤ አያገባህም ፤ አገሬን ለቀህ ውጣ ፤ ያለበለዚያም መኖርና መቆየት የምትችለው እኔ እስከፈቀድኩልህ ድርስ ብቻ ነው እየተባለ እኩልነትና ነጻነት እንዴት ሊመጣ ይችላል? ቤንሻጉል ጉምዝ ማሳያ ምሳሌ ነው። አማራውና ኦሮሞው አብሮ እንዳይኖር  የተተበተበው የጥላቻ ሰንሰለት መበጣጠስ ጅምሯል ሊባል ይችል እንደሁ እንጅ የመርዝ ሽንኮፉ ገና አልተቃጠለም። አማራ አርዶሃል እንዳትረሳው የሚል ሐውልት በረዥሙ አቁሞ ይቅር ተባብለናል ማለት ጅልነት ባይሆን እንኳ ቂል መሆን አልያም ሞኝነት ነው። አቶ ለማ መገርሳ እየውሰዷቸው ያሉ እርምጃዎች አበረታች ቢሆኑም ለዘመናት የተሰበከው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ግን ቢያንስ በተማረው ህብረተሰብ ዘንድ ፈጥኖ የሚወጣ አይደለም። ኦሮሞ ታላቅ ህዝብ ነው፤ በወዙ በጉልበቱ በሃብቱ የሚኖር፣ ሌላውን የሚያገል ኢፍትሓዊ የሆኑ እሰቶች የሉትም፤ በኦሮምያ ክልል ያሉ ከተሞች የሚተዳደሩባቸው ህጎች ግን የራሱን የቆየውን የደለበውን የገዳ ስርዓት እንኳ የማይዎክሉ ናቸው። ለዚህም በሌላ ጊዜ የየከትሞችን ኢፍትሀአዊ የሆኑ አንቀጾችን እንመለከታለን። የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገመንግስት ግን በሀገራችን ላሉ የዎንጀል ፍቃድ ወረቀቶች ማሳያ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። በተለይም በክልሉ አማራና ኦሮሞ የተገፉበት መንገድ በጣም አሳፋሪ ነው። ለጊዜው በክልሉ የኦሮሞ መፈናቀልና ሞት የለም ነገር ግን ኦሮሞውችም ቢሆኑ የክክልሉ ባለቤት መሆን አይችሉም ። በገፍ እየተገደለና እየተባረረ ያለው አሁንም አማራው ነው። ምክንያቱን ሊያውቁት የሚችሉት ህገመንግስቱን ያረቀቁትና ያጸደቁት ብቻ ናቸው። ስለዚህ የትግራይ ኦንላይንን ስጋት አሁን በግልጽ መረዳት የሚቻል ይመስለኛል። በጥናት ኦርኬስትሬት የተደረገው ህገ መንግስት ሌላ አገዛዝ ከመጣ እንድሚሰረዝ ያውቁታልና።ከእንግዲህ ውሸት አያስፈልግም ሲባልም እውነትን ወደ አደባባይ ማዉጣት አስፈላጊ  መሆኑን መዘንጋትም የለብንም። ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት ተቃዋሚ ነን ሲሉ የኖሩ ቡድኖች ሁሉ ከአገዛዙ ጋር አብሮ ለመስራትና እርቅን ለማዉረድ አዎንታቸውን ሲሰጡ ተመልክተናል፤ አይተንማል። መልካም የሚባል እርምጃ ሊባል ቢችልም ሁሉም ላይ ጥርጣሬ እንዲያጭርብን ሆኗል። ሁለት ነገር መደምደም ይቻላል። አንድም የበሰለ፣በድርድር የሚያምን፣ መሰረቱ የጸና፤ስሜታዊ ያልሆነ ተቃዋሚ አልነበረንም ወይም ተቃዋሚ መባላቸው የውሸትና የተንኮል ነበር ማለት ነው። ለዘመናት በደል ተፈጸመ እያለ ሲጮህ የኖረና አገዛዙን አንደ አውሬ እንድናየው ሲሰብክ የነበረ አገዛዙ ዘረኛ ነው እያለ እውነት የሚመስል ፕሮፓጋንዳ ሲነዛ የኖረ፣ አማራ በዘሩ ምክንያት ተፈናቀለ በማለት ሲያስተጋባ የኖረ ተቃዋሚ በየትኛው የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ ነው

ወደ አገር ቤት ለመግባት የወሰነው?ዛሬም ተንኮል ተንኮል የሚሸትት ነገር አለ። አገዛዙ እኮ አማራን በዘሩ ሳሳድድ ኖሬያለሁ፤ ያም ስህተት ነበር አላለም ፤ ይቅር በአርባ ጉጉ በአርሲና በሐረርጌ ገደሎች ከእነ ነፍሳቸው የተወረወሩትን ንጹሃን ደም ያፈሰሱትን አውሬዎች ወደ ፍርድ ማምጣቱና አሁን በቅርብ ከሰባ ስምንት ሺህ በላይ ምንም የማያውቁ ገበሬዎችን በደብዳቤ እንዲዎጡ ያዘዘው ሽፈራው ሽጉጤ ለፍርድ ማቅረቡ ቀርቶ አጥፍቻለሁ ብሎ ይቅርታ እንዲጠይቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ይቅርታና ፍቅር ስለተሰበከ ብቻ ተቃዋሚ ነኝ ባይ ጨዋታው አበቃ ማለት ነበረበትን?ትግራይ ኦን ላይን ላይ የወጣው ጽሑፍ እጅግ ብዙ እውነታዎችን የሚያሳይ ቀይ መብራት ነው። በሀገሪቱ ተደረገ የሚባለውን ለውጥ በስጋትም ይሁን በጠቃሚነቱ ምንም ያላለው ይህ የመረጃ ማእከል ከፍተኛ ስጋቱ የአማራ ብሐራዊ ንቅናቄ መመስረቱ ነው። ይህንን ድርጅት ዶክተር አብይ በአስቸኳይ እንዲያስቆሙትም ይማጸናል።አሁንም አንድ የተደበቀ ተቃዋሚ የሚባል ሁሉ የማያዉቀው ሴራ አለ ለማለት ያስደፍራል። ዶክተር አብይ እንደተባለው በፈርዖን እጅ ያደጉ መሴ ከሆኑ ከኢኮኖሚዉም ሆነ ከማህበራዊው እድገት በፊት ወተትና ማር ከምታዘንበው ምድር ይዘውን ከመግባታቸው በፊት ከተከተለንና ከታወጀብን ጦርነት አስቀድመው በአዋጂ እንዲያስመልጡን ያስፈልጋል። አስቀድመው በህገመንግስትና በተለያዩ ህጎች የታገዘውን የአማራ ማጽዳት ሂደት ያስቁሙት። እውነት ፤ ፍትህና ቅንንነት በታቸውን ይያዙ።

በቅርቡ ጋዜጠኛ ደሳለኝ ዶክተር አብይ ወደፊትም የግድያ ሙከራ ሊደረግባቸው ስለሚችል የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል በማለት የመከረውን ምክር በጥንቃቄ አዳምጨዋለሁ። በህዝቡ ዘንድ የተበተነዉን መሳሪያ መሰብሰብ እንዳለባቸው መከረ። በቀናነት ለሚያስብ ምክሩ እጅግ ማለፊያ ነው ።ጋዜጠኛ ተመስገን ለማለት የፈለገው ህወህት በርካታ የጦር መሳሪያዎችን ለአባላቱ ስለሰጠ ያ ጉዳት እንዳያደርስ በማሰብ ከቅንነት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አገዛዙ የጋዜጠኛ ደሳለኝን እውቅና በመጠቀም ጋዜጠኛው እንዳለዉም በሓይል ሳይሆን በዘዴ መሳሪያን ለመግፈፍ ቢሞክር ህወሃት የአማራዉን ህዝብ ትጥቅ ለማስፈታት የተለያዩ ሙከራውችን ማድረጉን መዘንጋት የለብንም። ከዚህ በኋላ ይህ የቀን እርድ የታወጀበት ማህበረሰብ ሁሉን በጥንቃቄ ማየት ይኖርበታል። በርካታ ነገሮችን መገንዘብ የሚገባን አሁን ነው። በአገርቤት ሚዲያዎች የግንቦት ሰባት፤ ኦነግና ሌሎችም የትጥቅ ትግል ያደርጉ የነበሩ ድርጅቶች ከመንግስት ጋር ለመታረቅና አብሮ ለመስራት መወሰናቸው እንደትልቅ ድል እየተነገረ ይገኛል። የእኔ ግንዘቤ ከብዙሃኑ ምናልባትም ሴናሪዮ ከማይገባቸው ቡድኖች ሊለይ ቢችልም ስጋቴን ማጋራት ግን እፈልጋለሁ። ለመሆኑ እነዚህ ድርጅቶች ነበሩ ወይ?በእርግጥ ግንቦት ሰባት የሚባል የታጠቀ ድርጂት ነበር ? ኦነግስ ከተዎሰኑ ፕሮፓጋንዲስቶች ውጭ መንግስትን ሊጥል የሚችል ሃይል ነበረው?ሌሎች ታጠቁ የሚባሉ ድርጅቶች በእርግጥ የመንግስት ስጋት ነበሩን?በማስተዋል ለተመለከተው መልሱ ቀላል ነው። ምናልባትም ሁሉንም ጊዜ ይፈታዋል። በ አጠቃላይ ለማለት የምፈልገው ብዙ ቢኖረኝም ለዛሬ እዚህ ላይ ላብቃ። ነገር ግን ጥያቄወቼን እንደሚከተለው ልሰንዝር ።የአማራ ድርጅቶችና እውነተኞቹ የዚህ ማህበረሰብ ተቆርቋሪዎች በዘዴ ዛሬም የሚገፉት ለምንድነው?ዶክተር አብይ የያዙት ለውጥ ስር ነቀልና እውነተኛ ይቅርታ የሚፈልጉ ከሆነ መንግስትዎ አማራን ለማግለል የተጠቀመበትን ዘዴ ሁሉ አምነው ይቀርታ ይጠይቁና አግላይ የሆኑ ህጎችን ሁሉ ይሻሩ፤ ከዚያም እውነተኛውን የአማራን ህዝብ ድጋፍ ባይፈልጉት እንኳ በሄዱበት ሁሉ ከእርስዎ ጋር ለመሆን የሚያግደው ተራራ አይኖርም።እግዚአብሔር አገራችንን ይባርክ!!

አዲስ ተስፋ

ሰኔ 2010 ዓም